# ሕልም ነውስ ቅዥት?

በአዕምሮ ማሰብ ወንጀል በሆነበት፣
ሕግ አራዊት ነግሦ ፍትሕ በጠፋበት፤
የፈጠራ ሥራ በተወገዘበት፣
በኢትዮጵያ ምድር በተፈጠርንበት፤
አለሁኝ ማለቱ ሕልም ነውስ ቅዥት።
ከረሃብ ከደህነት ከቶንም ሳንወጣ፣
ስንት ሕይወት ፈጠርን ስንትስ ሕይወት ጠፋ?
እንደፈረስ ልጓም እንደአህያ ቀርቃባ፣
ጭነቱ ሲራገፍ ከጥሬ ለቀማ፣
ከብረሃን ይልቅ ተመርጦ ጭለማ፣
ኖርኩኝ መባል አይቀር ኑሮ ተባለና።
አዕምሮን ተጠቅመን ሁኔታን ካለወጥን፣
መነጣጠል ትተን በአንድነት ካልሠራን፣
በዘዴ በጥበብ ካልተገኘን ልቀን፤
ቂም በቀል ጥላቻን ዘዴ ካደረገው፣
ከወያኔ ዲሪቶ ሂዶ መለጠፍ ነው።
አለሁኝ ማለቱ ሕልም ነውስ ቅዥት፣
በአዕምሮ የሚያስብ ፍጡር በበዛበት፣
ነገሩ ሆነና የተገላቢጦሽ፣
አህያ ወደ ሊጥ ውሻ ወደ ግጦሽ።

ታደለ መኩሪያ

EthioLion.com